**ለ2022 የዓለም-አቀፉ የቻይንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች**

**ክርስቶስን እንደ የጺጋ መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ መቀበል**
**የሕይወት ዘመን ሁሉ፣ የማያቋርጥ ጉዳይ ነው፤**
**ዕለት ዕለት እግዚአብሔር የጺጋን መንፈስ አቅርቦት አትረፍርፎ ሲሰጥና**
**እኛም የጺጋን መንፈስ ባለማቋረጥ ስንቀበል ሳለን**
**ድንቅ መለኮታዊ መተላለፍ መከናወን አለበት።**

**በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ በእግዚአብሔር ጸጋ ሥር የሆነው**
**የአዲስ ኪዳን አማኞች ኑሮ—**
**በሂደት ያለፈውንና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ**
**እንደ ጸጋ የመለማመድ ጥቅል ኑሮ—**
**ሕይወታዊ የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ይጠናቀቃል።**

**ጸጋ የሸክማችን ተሸካሚ የሆነው ክርስቶስ ነው፣ ይህም ጸጋ**
**በመከራዎቻችን፣ በገደቦቻችን እና በድካሞቻችን ይበዛልናል፤**
**ሸክሞች ይበልጥ በኖሩን መጠን ክርስቶስን እንደ ጸጋ**
**ለመለማመድ የበለጡ እድሎች ይኖሩናል።**

**በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር እንደ የእግዚአብሔር ጽድቅ መጠናቀቅ**
**አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለመሆን በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ**
**የላቀው እና ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ የእግዚአብሔር ጸጋ ፍሬ**
**የእግዚአብሔር ድንቅ የጥበብ ሥራ የሆነው የክርስቶስ አካል ነው፤**
**ለድሰታችን የእግዚአብሔር የራሱ ብልጥግናዎች ሁሉን ገደብ ያልፉሉ፣**
**ለዘላለምም በገሃድ እንደ አውደ ርዕይ ይታያሉ።**

*© 2022 Living Stream Ministry*

**የዓለም ዓቀፉ የቻይንኛ ተናጋሪዎች ኮንፈረንስ**
**የመልእክቶች አውትላይኖች**
**የካቲት 11-13፣ 2014**

**አጠቃላይ ርዕስ፡-**
**የእግዚአብሔር ጸጋ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ**

*መልእክት አንድ*

**የእግዚአብሔር ጸጋ ታላቅ ትርጉም**
**በአዲስ ኪዳን እንደተገለጠው**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ ዕብ. 10፡29፤ 1 ጴጥ. 5፡10፤ ኤፌ. 1፡5-6፤ 2፡7-8፤ ራእ. 22፡21

I. **የእግዚአብሔር ጸጋ ታላቅ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው—ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ ኤፌ. 2፡7፤ ራእ. 22፡21፡-**

ሀ. በአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ውስጥ ጸጋ ታላቁ እውነት እና ከፍተኛው መገለጥ ነው—ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ ዕብ. 10፡29፤ 1 ቆሮ. 15፡10፤ ፊልጵ. 4፡23፤ ራእ. 22፡21።

ለ. በአዲስ ኪዳን እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ምን እንደሆነ መረዳት ከፈለግን፣ ግልጽ የሆነ አጠቃላይ የአዲስ ኪዳን እይታ ያስፈልገናል።

II. **በአዲስ ኪዳን መሠረት፣ ጸጋ በእርግጥ እግዚአብሔር ለድሰታችን የሆነው ነገር ነው—ዮሐ. 1፡16-17፤ 2 ቆሮ. 12፡9፡-**

ሀ. ጸጋ እግዚአብሔር በአስተምህሮ ሳይሆን እግዚአብሔር በልምምዳችን ነው፣ ምክንያቱም ጸጋ ክርስቶስ ከሆነው ነገር ሁሉ ጋር እግዚአብሔር በክርስቶስ ለድሰታችን ነው፤ ይህም ሕይወትን፣ ብርታትን፣ ምቾትን፣ ዕረፍትን፣ ብርሃንን፣ ጽድቅን፣ ቅድስናን፣ ኃይልን እና ሌሎቹን መለኮታዊ ባሕሪያት ያካትታል።

ለ. ጸጋ በዋናነት እግዚአብሔር ለእኛ የሚሠራው ሥራ አይደለም፤ ጸጋ ሦስታንዱ አምላክ ራሱ ወደ ማንነታችን ውስጥ መታደሉ እና ለድሰታችን ልምምዳችን መሆኑ ነው—13፡14።

ሐ. በመለኮታዊው ሥላሴው በሂደት በማለፍና በመጠናቀቅ እንዲሁም በአማኞች ውስጥና መካከል በመንቀሳቀስና በመኖር፣ እንደ የሦስታንዱ አምላክ ሥጋ መልበስ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ጸጋ ታሪክ ነው—ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ ራእ. 22፡21።

III. **ጸጋ ሦስታንዱ አምላክ አካል በመልበሱ በሦስት ገጽታዎች የእርሱ መታየት ነው —አብ፣ ወልድ እና መንፈስ—2 ቆሮ. 13፡14፤ ዘኍ. 6፡22-27፤ መዝ. 36፡8-9፡-**

ሀ. ጸጋ በአብ እንደ ምንጭ፣ በወልድ እንደ ንጥረ-ነገር እና በመንፈስ እንደ መተግበር ሦስታንዱ አምላክ በተሠግዎው ወደ አማኞች ውስጥ ይታደል ዘንድ ነው—2 ቆሮ. 13፡14፡-

1. ሁሉ ነገራችን ይሆኑ ዘንድ የጸጋ ምንጭ፣ የጸጋ ንጥረ-ነገር እና የጸጋ መተግበር ከመለኮታዊው ሥላሴ ሦስቱ ማንነቶች የሚመነጩ ናቸው—ማቴ. 28፡19።
2. በመለኮታዊው እደላ ጸጋ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የክርስቶስ ጸጋ እና መንፈስ የሆነው የእርሱ ጸጋ ይባላል—1 ቆሮ. 15፡10፤ 2 ቆሮ. 1፡12፤ 8፡1፣ 9፤ 9፡14፤ 12፡9፤ 13፡14፤ ዕብ. 10፡29።

ለ. ጸጋ ከመለኮትነትና ከሰብዕና ጋር አምላክ-ሰው የሆነው፣ በሰብዕና ኑሮ ያለፈው፣ የሞተው፣ ከሞት-የተነሣው እና ወደ ዕርገት ውስጥ የገባው የእግዚአብሔር አካል መልበስ ነው፤ አሁን እርሱ በውስጣችን የሚያድረው ሕይወት-የሚሠጠው መንፈስ ነው—1 ቆሮ. 15፡45፤ 6፡17።

ሐ. ጸጋ እንደሰተው ዘንድ ለእኛ በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ነው—ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ 1 ጴጥ. 5፡10፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ዕብ. 10፡29፤ 1 ቆሮ. 15፡10፣ 45፤ ራእ. 22፡21።

መ. በሂደት ሳያልፍ ሦስታንዱ አምላክ ጸጋ ሊሆንልን ባልቻለ ነበር—ዮሐ. 1፡14፤ 1 ቆሮ. 15፡45፡-

1. አብ አካል የለበሰው በወልድ ነው፣ ወልድ እውን የሚሆነው በመንፈስ ነው፣ መንፈስም ለድሰታችን እንደ ጸጋ ወደ ውስጣችን ይገባል—ዕብ. 10፡29።
2. በመለኮታዊው ሥላሴው እርሱን እንደ ሁሉ ነገራችን እንደሰተው ዘንድ፣ እንደ ጸጋ እድል ፈንታችን ለመሆን፣ በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ወደ ውስጣችን ያድላል—2 ቆሮ. 13፡14።

IV. **አምላካችን እና አባታችን "በውድ ልጁም... ጸጋው[ን]..." ሰጠን—ኤፌ. 1፡6፡-**

ሀ. እግዚአብሔር ለእኛ ጸጋን መስጠቱ ትርጉሙ የእርሱ ጸጋና ሞገስ ትኩረት እንሆን ዘንድ፣ ማለትም እግዚአብሔር ለእኛ የሆነውን ሁሉ እንደሰት ዘንድ እኛን በጸጋ ሥፍራ ውስጥ ማስቀመጡ ነው—ቁ. 6፡-

1. በጸጋ ሥፍራ ውስጥ ላይ ስላለን እና የጸጋው ትኩረት ስለሆንን እግዚአብሔር በእኛ ደስ ይለዋል።
2. እግዚአብሔር በእኛ ይደሰታል፣ እኛ በእርሱ ደስተኞች ነን፣ በስተመጨረሻም የጋራ ድሰታ አለ፤ እኛ እርሱን እንደሰተዋለን፣ እርሱም እኛን ይደሰተናል።

ለ. ውድ የተባለው እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት የእግዚአብሔር ውድ ልጅ ነው—ማቴ. 3፡17፤ 17፡5፡-

1. ውድ በሆነው በእርሱ ጸጋ ተሰጥቶናል፣ የእግዚአብሔር ሞገስ ትኩረትና ደስታ ተደርገናል—ኤፌ. 1፡6።
2. ይህን አይነት ትኩረት እንዳገኙ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደሰተዋለን፣ እግዚአብሔርም በጸጋው፣ ደስ በሚሰኝበት በውድ ልጁ እኛን ይደሰተናል፤ ለእርሱ ውድ በሆነው በእርሱ እኛም ደግሞ ደስ የምናሰኘው እንሆናለን—ማቴ. 3፡17፤ 17፡5።

**V. በኤፌሶን 2፡8 ጳውሎስ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም" ይላል፡-**

ሀ. ጸጋ እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን መታደሉ ነው፤ ስለዚህ በጸጋ መዳን ማለት በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ወደ ውስጣችን በመታደሉ መዳን ነው።

ለ. የሚያድነው ጸጋ ራሱ እግዚአብሔር በክርስቶስ ወደ ውስጣችን መሠራቱ እንደሆነ ኤፌሶን ይገልጣል፤ ስለዚህ በጸጋ መዳን በእርግጥ ትርጉሙ ሦስታንዱ አምላክ ወደ ውስጣችን በመታደሉ መዳን ማለት ነው።

ሐ. በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ወደ ውስጣችን ሲታደል በልምምዳችን የሚያድነው ጸጋ ይሆንልናል—2 ቆሮ. 13፡14።

**VI. "የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ" እግዚአብሔር አስቀድሞ ልጆች እንድንሆን ወስኗል—ኤፌ. 1፡5-6፡-**

ሀ. ክብር እግዚአብሔር ሲገለጥ ነው (ዘጸ. 40፡34)፤ *የጸጋው ክብር* የሚለው ሃረግ፣ እንደ ድሰታችን ራሱ እግዚአብሔር የሆነው የእግዚአብሔር ጸጋ እግዚአብሔርን እንደሚገልጥ ያመለክታል።

ለ. እግዚአብሔር እኛን አስቀድሞ ልጆች እንድንሆን መወሰኑ በጸጋው የሆነው መገለጡ ይመሰገን ዘንድ፣ ማለትም፣ የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ነው—ኤፌ. 1፡5-6።

**VII. "በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት" እግዚአብሔር ያሳየናል—2፡7፡-**

ሀ. በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት እግዚአብሔር በጸጋው አድኖናል፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ለእኛ የተሰጠን እንዲህ ባለ ቸርነት ነው—ቁ. 7፤ ሮሜ 2፡4።

ለ. የእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነቶች፣ ለልምምዳችን እና ለድሰታችን ወደ ውስጣችን የሚታደሉት የራሱ የእግዚአብሔር ባለጠግነቶች ናቸው፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነቶች እያንዳንዱን ወሰን ያልፋሉ።

ሐ. በሚመጡ ዘመናትም—በሺው ዓመት መንግሥት እና በወደፊት ዘላለም—እግዚአብሔር ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ለመላው አጽናፍ-ዓለም ያሳያል—ኤፌ. 2፡7።

© 2022 Living Stream Ministry